# ምድብ ሦስት (ከ4ኛ — 6ኛ) ክፍል

## 38 ኛ ሳምንት

## የሐዋርያትን እግር ማጠብ

**ዓላማ**

- ስለትኅትና እና በትኅትና ስለሚገኝ ክብር መማር

**የሚጠና ጥቅስ**

- *"እናንተ ደግሞ እርስ በእርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል።"* ዮሐ. 13፣14

**ምንባብ**

- ዮሐ. 13፣1-17

**መግቢያ**

- ዛሬ የምንማረው ትምህርት ጌታ የመጨረሻውን እራት ባደረገባት- የጸሎት ሐሙስ ዕለት የተፈጸመ ታሪክ ነው፤
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ምን ማድረግ እንዳለባቸው በማስተማር ብቻ ሳይሆን፣በድርጊትም ምሳሌ ሆኖ አስተምሯቸዋል።

ከዚህ ቀጥሎ የምንመለከተው የትኅትና ጥቅም እንዴት እንዳስተማረና ሌሎችን ስለማገልገል ነው።

**ትምህርቱ**

- በጸሎተ ሐሙስ ማታ፤ የፋሲካን እራት ከበሉ በኋላ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመታጠቢያ ውኃ አድርጎ፣ማበሻም ጨርቅ ይዞ የደቀመዛሙቱን እግር ማጠብ ጀመረ።ቅዱስ ጴጥሮስ ወደ ተባለው ስምዖን ሲደርስም ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታና መምህሩ ስለሆነ *"አታጥበኝም"* አለ።ጌታችን ግን *"እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቅም በኋላ ግን ታስተውለዋለህ.... ካላጠብሁህ ከእኔ ጋር እድል የለህም"* ብሎ መለሰለት።ጴጥሮስም ለመታጠብ እሺ አለ።
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀመዛሙቱን እግር ካጠበ በኋላ እንዲህ አላቸው ***"ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁ እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ እንዲሁ ነኝና መልም ትላላችሁ እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ እናንተ ደግሞ እርስ በእርሳችሁ ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል። እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችዋለሁና... ይህን ብታውቁ ብታደርጉትም ብፁዓን ናችሁ።"***
- ጌታችንም አንዱ ሌላውን በትኅትና እንዲያገለግሉ አስተማራቸው፣ይሄንን ምሳሌም በስቅለቱ ዋዜማ አሳያቸው።
- ይህ ከመሆኑ በፊት አንድ ቀን ደቀመዛሙርቱ ከመካከላቸው የሚበልጥ ማን ነው? ብለው ተከራክረው ነበር።ጌታችንም *"ከእናንተ ታላቅ የሆነ እንደ ትንሽ ያገልግል፤ ገዢም እንደ ባርያ ያገልግል።"* አላቸው።አሁን ደግሞ ትኅትናን በተግባር አስተማራቸው።

**መደምደሚያ**

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀመዛሙርቱን እግር በጸሎተ ሐሙስ ሲያጥብ እርስ በርሳቸው እንዲህ እንዲያደርጉ አስተምሮቸዋል። ታላቅ ለመሆን የሚፈልግም እንደ አገልጋይ እንዲሆን መከራቸው።
- በመታዘዝ በመልካምነት ለጓደኞቻችን፣ለመምህሮቻችን፣ ለወንድሞቻችን፣ ለእህቶቻችን እና ለቤተሰቦቻችን የምናደርገው መታዘዝና መልካምነት በመንፈሳዊ ግብረ ገብነት በእግዚአብሔር ፊት የሚቆጠር ነው።

**ጥያቄዎች**

1. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ትኅትና ለማስተማር ምን አደረገ?
2. እግሩን እንዳይታጠብ መጀመሪያ የከለከለው ደቀመዝሙር ማን ይባላል?
3. ከመካከላቸው ማን እንደሚበልጥ ሲጠይቁት ጌታችን ምን ብሎ መለሰላቸው?
4. የፋሲካ እራት ምንድን ነው? የመጨረሻው እራት ምንድን ነበር?
5. ለቤተቦቻችሁና ለጓደኞቻችሁ የምታደርጉትን የመታዘዝ ሥራ ዘርዝሩ።

**ይቆየን።**